የሰ/መ/ቁ. 55081

ጥቅምት 18 ቀን 2003ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሪት ራሔራ ሥነፀሐይ - ጠበቃ አስረስ ባያው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መስፍን ታምራት - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች የፍርድ ባለመብት የሆኑበትን እዳ ለማስከፈያ እንዲሆን የፍርድ ባለእዳው የተጠሪው ንብረት የሆነ ቤት እንዲሸጥላቸው አመልካች አመልክተዋል፡፡ ቤቱ በፍርድ ባለእዳው ልጅ ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ስሙ ተዛውሮና ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪ ቤቱን የእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ ያደረጉት ድርጊት በመሆኑ በልጃቸው ተማሪ ማራማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ንብረት ተሸጦ ፍርዱ እንዲፈፀምልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውል የጠየቁት ቤት በፍርድ ባለ እዳው ስም ሳይሆን በተማሪ ማሪማዊት መስፍን ስም የሚገኝ በመሆኑ አፈፃፀሙን በቤቱ ላይ ማስቀጠል አይቻልም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች የፍርድ ባለእዳ የሆነው ተጠሪ ቤቱን ለእዳ መክፈያ እንዳይሆን ለማሸሽ በማሰብ ምንም አይነት ሐብት ለሌላት አካለ መጠን ላልደረሰች ልጁ የቤቱን ስመ ንብረት በማዛወር የፈፀመው ተግባር መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የማራማዊት መስፍን ነው፡፡ ለዚህም ቤቱ የማራማዊት መስፍን መሆኑን የሚያረጋግጥ ውልና የቤቱ ክፍያ የተከፈለባቸው ወርሀዊ ደረሰኞች ስላሉ ቤቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር የተገለፀው ሲሆን ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ የሆነበትን ገንዘብ ለመክፈል ጥረት በሚደረግበት ጊዜ ቤቱ የተጠሪ ልጅ በሆነችው ህፃን ማራማዊት መስፍን ስም የተዛወረ መሆኑ የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡ የቤቱ ባለቤት ናት ቤቱም በስሟ ተመዝግቧል የምትባለው ማራማዊት መስፍን ህፃን መሆኗን የስር ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሰው የንብረት ባለቤት የሚሆነው በጉልበቱ በፈጠራ ችሎታው ወይም በገንዘቡ ንብረቱን ያፈራው ሲሆን እንደሆነ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ በተጠሪና በተጠሪ ባለቤት በወ/ሮ አለም ዘውዱ ዘርፉ ስም ተመዝግቦ የነበረው ቤት በህፃን ልጃቸው በህፃን ማራማዊት መስፍን ስም አዛውረው ቤቱን በህፃን ማራማዊት ስም አስመዝግበው መገኘታቸው ብቻውን ህፃን ማራማዊት መስፍን የቤቱ ባለሐብት ናት ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን እዳ መክፍያ እንዳይሆን ቤቱን በራሷ መንገድ ሰርታ ባገኘችው የገቢ ምንጭ የገዛችው ስለመሆኗ ሳያረጋግጥ የንብረቱ በህፃን ልጅ ስም በማዛወር ለፍርድ ማስፈፀሚያነት ንብረቱ እንዳይውል ለማሸሽ የሞከረ መሆኑን የሚያመለክት ተግባር ነው፡፡

የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው ንብረቱ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እዳይውል አካለ መጠን ባልደረሰ ህፃን ልጁ ስም እያዛወረ መልሶ ንብረቱን በሞግዚትነት የሚያስተዳድርበት የሚሸጥበትና የሚለውጥበትን ሁኔታን ህጋችን አይፈቅድም፡፡ ባለእዳው መክፈል የሚገባውን እዳ ባለመክፈል በአጭበርባሪነት የሚፈጽማቸውን ተግባራት የፍርድ ባለመብት ወይም ገንዘብ ጠያቂው የመቃወምና እዳውን ላለመክፈል ያደርገው ተግባር መሆኑን ለማሳየት በማጭበርበር የተሰራው ስራ ዋጋ እንዳይኖረውና ባለእዳው እዳውን እንዲከፍል ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1895 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1896 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መዝገብ በተጠሪና በአመልካች ስም የነበረውን ቤት ተጠሪ በህፃን ልጁ ለማራማዊት መስፍን ስም ማዛወሩ ንብረቱ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዳይሆን ለማድረግ የተፈፀመ የማጭበርበር ተግባር ነው በማለት አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. በመጀመሪያ በተጠሪና በባለቤታቸው ወ/ሮ ዓለም ዘውድ ዘርፉ በአሁኑ ጊዜ በህፃን ማሪማዊት መስፍን ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት አመልካች በፍርድ ያስወሰኑትን ገንዘብ ማስፈፀሚያ እንዲሆንና የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሐራጅ በማሸጥ እንዲያስፈጽም ጉዳዩን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

ሶ/በ